የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሰላሳ ሶስተኛ ዓመት ቁጥር ፻፲፬
አዲስ አበባ ሰኔ ፲፱ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

33 Year No 114
Addis Ababa 19th day of June 2026

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፴/፪ሺ፲፰

ከሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም ከመኝታ አገልግሎት ማዘጋጃቤታዊ ታክስ ለመጣል የወጣ ደንብ

ገጽ .....፬ሺ፪፻፭

CONTENT

REGULATION NUMBER 204/2026

A REGULATION TO PROVIDE FOR IMPOSING MUNICIPAL TAX ON ACCOMMODATION SERVICES OF HOTELS AND SIMILAR SERVICE-PROVIDING ESTABLISHMENTS

Page 4205

ደንብ ቁጥር ፪፻፴/፪ሺ፲፰

ከሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም ከመኝታ አገልግሎት ማዘጋጃቤታዊ ታክስ ለመጣል የወጣ ደንብ

የአዲስ አበባ ከተማ ደረጃውን የጠበቀ መሰረተ ልማት በመገንባት ለቱሪስት መዳረሻነት ተመራጭ እየሆነች በመምጣቷ ሆቴሎችና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከጎብኚዎች ገቢ በመሰብሰብ ልማትን ለማፋጠን የሚያስችል አቅም ያለው መሆኑ በመታመኑ፤

ሆቴሎችና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከተማዋ በምታመነጨው ኢኮኖሚ ልክ ለገቢው እያደረገ የሚገኘውን አስተዋጽኦ ለማሻሻል፤ ኢ-ፍትሀዊነትን በመቀነስ ህጋዊነት ለማስፈን እና በተወሰኑ ታክስ ገቢ ላይ ትኩረት ያደረገውን የከተማዋን የገቢ አሰባሰብ በማሻሻል የማዘጋጃ ቤታዊ ገቢን አሁን ካለበት አነስተኛ ድርሻ የገቢ መሰረት በማስፋት የከተማዋን የገቢ አቅም [illegible] በማስፈለጉ፤

REGULATION NUMBER 204/2026

A REGULATION TO PROVIDE FOR IMPOSING MUNICIPAL TAX ON ACCOMMODATION SERVICES OF HOTELS AND SIMILAR SERVICE-PROVIDING ESTABLISHMENTS

WHEREAS, it is believed that hotels and such other service providing establishments have the potential to collect revenues from visitors and accelerate development endeavours as Addis Ababa has become a preferred tourist destination through the construction of standard infrastructure;

WHEREAS, it has been found necessary to improve the revenue generating capacity of the city through expanding the tax base of municipal revenue from its current low proportion to the economy through improving the contributions of hotels and such other service providing establishments in its revenue generation to the economy, ensuring legality by reducing unfairness, and improving the revenue collection of the city that focuses itself in limited tax revenues;

ከተማዋ ለቱሪስትና ለነዋሪዎቿ ምቹ የማድረግ የተለያየ መስዕብ ያለው የጉብኝትና የመዝናኛ ቦታዎችን የማልማት፣ መሰረተ ልማትና ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን የማዘመን እና ዘላቂነቱ የተረጋገጠ ለማድረግ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ በማስፈለጉ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ምክርቤት በአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፪፻፶፱ (እንደተሻሻለ) አንቀፅ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተራ ፊደል (ሠ) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "ከሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም ከመኝታ አገልግሎት ማዘጋጃ ቤታዊ ታክስ ለመጣል የወጣ ደንብ ቁጥር ፪፻፬/፪፻፲፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

የቃሉ ወይም የሐረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. "ከተማ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. "የከተማ አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. "አዋጅ" ማለት እንደአግባቡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፫፬/፪፻፲፭ እና የታክስ አስተዳደር አዋጅ ፱፻፹፫/፪፻፷ ነው፤

፬. "ቢሮ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ነው፤

፭. "የታሪፍ ምጣኔ" ማለት ማንኛውም ሰው የሚፈለግበትን የግብር እና የአገልግሎት ክፍያዎችን መጠን ለማስላት የሚያገለግል ነጠላ ተመን ነው፤

፮. "የመኝታ ክፍል አገልግሎት ታክስ ክፍያ" ማለት የሆቴል ወይም መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የመኝታ ክፍልን ለአንድ ቀን በሚያስከፍሉት ዋጋ ክፍያ ላይ ተሰልቶ በተጨማሪ የሚሰበሰብ ገቢ ነው፤

WHEREAS, it has been found necessary to have additional source of revenue to make the city conducive for tourists and its residents, develop diverse tourist attractions and recreational sites, modernize infrastructure and various services, and ensure the sustainability of the thereof;

NOW, THEREFORE, in accordance with Paragraph (e) of Sub-Article (1) of Article 14 of the Revised Charter of the Addis Ababa City Government Proclamation Number 361/2003, the Addis Ababa City Council has issued this Regulation.

Part One
General Provision

1. Short Title

This Regulation may be cited as: "**Imposing Municipal Tax on Accommodation Services of Hotels and Similar Service-Providing Establishments Regulation Number 204/2026.**"

2. Definition

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1. **"City"** means the Addis Ababa city;
2. **"City Government"** means the Addis Ababa city Government;
3. **"Proclamation"** means the Addis Ababa City Government Executive Organs Re-establishment and to Specify the Powers and Duties of the thereof Proclamation Number 84/2023 and the Tax Administration Proclamation Number 983/2016, as the case may be;
4. **"Bureau"** means the Addis Ababa City Government Revenues Bureau;
5. **"Tariff Rate"** means a single rate that is used to calculate the amount of tax and service fees required from any person;
6. **"Accommodation Service Tax payment"** means an additional revenue collected based on the daily rate calculated for a room in which a hotel or similar service-providing establishment demands;

Addis Ababa City Administration Revenues Bureau

፯. "ሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም" ማለት፣ ሆቴል፣ ሪዞርት፣ ሞቴል፣ ፔንሲዮን፣ እንግዳ ማረፊያ እና ሎጅ ያካትታል፤

፰. "ሆቴል" ማለት የመኝታ፣ የምግብ፣ የመጠጥና እንደ አስፈላጊነቱም የመዝናኛ፣ ስብሳባና መሰል አገልግሎቶችን ለቱሪስቶችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች የሚያቀርብ ድርጅት ነው፤

፱. "ሪዞርት" ማለት የመኝታ፣ የምግብ፣ የመጠጥና እንደ አስፈላጊቱም የመዝናኛ፣ ስብሰባና መሰል አገልግሎቶችን ለቱሪስቶችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች የሚያቀርብ ሆኖ በአቅራቢያው የቱሪስት መስዕብ ያለው ነው፤

፲. "ሞቴል" ማለት የመኝታ፣ የመኪና ማቆሚያና እንደ አስፈላጊነቱ የምግብና የመጠጥ አገልግሎቶችን በከተማ፣ ከከተማ ውጭና በአውራ ጎዳና ዳር ላይ ለቱሪስቶችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች የሚያቀርብ ድርጅት ነው፤

፲፩. "እንግዳ ማረፊያ" ማለት ሳሎን፣ መኝታ ቤት፣ የምግብ ማዘጋጃ፣ መታጠቢያ ክፍሎች፣ እንዲሁም የቤት ዕቃዎች ለእያንዳንዱ ክፍል ተሟልተውለት መስተንግዶና የምግብ አገልግሎት ሳይጨምር ከነሙሉ ዕቃው ለእንግዶች የሚከራይ ተቋም ነው፤

፲፪. "ፔንሲዮን" ማለት የመኝታና እንደ አስፈላጊነቱ የቁርስ አገልግሎትን ለቱሪስቶችና ለሌሎችም ተጠቃሚዎች የሚያቀርብ ተቋም ነው፤

፲፫. "ሎጅ" ማለት በተፈጥሮ አካባቢዎች አቅራቢያ የሚገኝ በአካባቢው ቁሳቁሶች የተገነባ የምግብ፣ የመጠጥ፣ የመኝታ እና ሌሎች የመዝናኛ አገልግሎቶች የሚሰጥ ተቋም ነው፤

፲፬. "የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም መኝታ ክፍል ይዞታ" ማለት አንድ ሆቴል ወይም መሰል ተቋም ለመኝታ አገልግሎት ከሚያከራያቸው ክፍሎች በአንድ ቀን በተገልጋይ የሚያዙ ክፍሎች ብዛት ነው፤

፲፭. "ባለ ኮከብ ሆቴል" ማለት አግባብ ባለው አካል አማካኝነት ሆቴሎች ከሚያቀርቡት አገልግሎት ጥራትና ቅንጡነት መነሻ በማድረግ በሚሰጠው ደረጃ የሚወሰን ሲሆን እነሱም ከባለ ፩ ኮከብ ሆቴል እስከ ባለ ፯ ኮከብ ሆቴል የሚመደቡ ናቸው፤

7. **"Hotel and Similar Service Providing Establishments"** means any facility that includes hotels, resorts, motels, pensions, guest houses, and lodges;

8. **"Hotel"** means an establishment that provides accommodation, food, beverage, and, as it deems necessary, recreation, meeting, and such other similar services to tourists and other users;

9. **"Resort"** means an establishment that provides accommodation, food, beverage, and, as it deems necessary, recreation, meeting, and such other similar services to tourists and other users, having a nearby tourist attraction;

10. **"Motel"** means an establishment located within the city, outside the city, or along highways that provides accommodation, parking, and, as it deems necessary, food and beverage services to tourists and other users;

11. **"Guest House"** means an establishment with a living room, bedroom, kitchen, bathrooms, and fully equipped furniture for each unit, rented to guests with all its facilities, except the provision of hospitality and food services;

12. **"Pension"** means an establishment that provides accommodation and, as it deems necessary, breakfast services to tourists and other users;

13. **"Lodge"** means an establishment which is located near natural environments and constructed with local materials and provides food, beverage, accommodation, and other recreational services;

14. **"Hotel and Similar Service Providing Establishments Room Occupancy Status"** means the number of rooms rented out for accommodation to users in a single day by a hotel or similar establishment;

15. **"Star Hotel"** means a rating determined by the relevant authority based on the quality of services and luxury provided by hotels, and they are categorized from 1-star hotel to 7-star hotel;

Addis Ababa City Administration Revenues Bureau

፲፮. "ባለቤት" ማለት ሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም ባለንብረት ወይም የመኝታ ክፍሎችን ተከራይቶ የመኝታ አገልግሎት የሚሰጥና የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም መኝታ ክፍል ይዞታ ክፍያ የሚሰበስብና ለቢሮው ገቢ የሚያደርግ ሰው ነው፤

፲፯. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፰. በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል።

፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የመኝታ አገልግሎት በሚሰጡ የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

<u>ክፍል ሁለት</u>
<u>የሆቴልና መሰል አግልግሎት ሰጪ ተቋም የመኝታ አገልግሎት ታክስ ስለመጣልና ስለመመዝገብ</u>

፬. <u>የሆቴልና መሰል ተቋም መኝታ ክፍል አገልግሎት ሰጪ ድርጀቶች አይነት እና ደረጃ</u>

ማንኛውም ሆቴል አግባብ ባለው አካል በወጣው መስፈርት መሰረት እንደ አገልግሎት አሰጣጡ በደረጃና ዓይነት እንደሚከተለው ይከፈላል፡-

ሀ) ባለ ፭ እና ከዚያ በላይ ኮከብ ሆቴል፣

ለ) ባለ ፬ ኮከብ ሆቴል፣

ሐ) ባለ ፫ ኮከብ ሆቴል፣

መ) ባለ ፪ ኮከብ ሆቴል፣

ሠ) ባለ ፩ ኮከበ ሆቴል፣

ረ) ኮከብ የሌላቸው ሆቴሎች ተብለው በደረጃ ሊመደቡ ይችላሉ፤

፩. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለጠው እንደተጠበቀ ሆኖ የመኝታ አገልግሎት የሚሰጡ ሌሎች ሆቴሎች በዓይነት እንደሚከተለው ሊመደቡ ይችላሉ፤

ሀ) ሪዞርት፣

ለ) ሎጅ፣

ሐ) ሞቴል፣

መ) እንግዳ ማረፊያ እና

ሠ) ፔንሲዮን።

16. **"Owner"** means a person who owns a hotel or similar service-providing establishment or rents rooms to provide accommodation services, and collects the accommodation room occupancy fee of the hotel or a similar establishment and transfers it to the bureau;

17. **"Person"** means any natural or juridical person;

18. In this Regulation, any expression in the masculine gender shall also include the feminine gender.

3. <u>Scope of Application</u>

This Regulation shall apply to hotels and similar service-providing establishments providing accommodation services within the Addis Ababa city.

<u>Part Two</u>
<u>Imposition of Accommodation Tax on Hotels and Similar Service-Providing Establishments and Registration</u>

4. <u>Types and Grades of Hotels and Similar Accommodation Service-Providing Establishments</u>

Any hotel shall be categorized by grade and type in the following manner according to its service delivery as per the criteria issued by the relevant authority:

A. 5-star hotel and above that;
B. 4-star hotel;
C. 3-star hotel;
D. 2-star hotel;
E. 1-star hotel;
F. Hotels with no star

1. without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, other hotels that provide accommodation service shall be categorized by type as follows:

A. Resort;
B. Lodge;
C. Motel;
D. Guest House; and
E. Pension

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ Addis Ababa City Administration Revenues Bureau

፭. ስለምዝገባ

የሆቴልና መሰል ተቋማት መኝታ ክፍል አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን በሚከተለው ሁኔታ ተለይተው ይመዘገባሉ፡-

፩. የንግድ ድርጅት የሆኑ ሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የምንዳና ደመወዝ እና ኪራይ ግብር በሚከፍሉበት የከፍተኛ እና መካከለኛ የገቢ መስሪያ ቤት ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ለመኝታ አገልግሎት ታክስ ከፋይነት በአካል በመቅረብ መመዝገብ አለባቸው፤

፪. ግለሰብ የሆቴልና መሰል ተቋማት ባለቤት ግብር ከፋዮች የንግድ ትርፍ ግብራቸውን በሚያሳውቁበት የገቢ መስሪያ ቤት ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ለመኝታ አገልግሎት ክፍያ በአካል በመቅረብ መመዝገብ አለባቸው፤

፫. የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም መኝታ አገልግሎት ሰጪዎች ለመኝታ ያዘጋጁት ክፍል ብዛት እና የአንድ ቀን ዋጋ ዝርዝር መረጃ ግብር በሚያሳውቁበት የገቢ መስሪያ ቤት ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት በኩል በተዘጋጀው የመመዝገቢያ ቅጽ መሙላት እና ማሳወቅ አለባቸው፡፡

፮. የክፍያ መሠረት እና የታክስ ምጣኔ

፩. የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም መኝታ ይዞታ ክፍያ አንድ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ለአንድ ቀን የሚከፍለው የመኝታ ክፍል ክፍያ ዋጋ ነው፤

፪. የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም ውስጥ ያለው የአንድ የመኝታ ክፍል ዋጋ በሆቴሉ የሚቀርበውን የምግብ ዋጋ እና በሆቴሉ ለተጠቃሚው የሚሰጠውን የግል አገልግሎት ወጪን አያካትትም፤

፫. የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም የመኝታ የአገልግሎት ክፍያ ስሌት ከተጨማሪ እሴት ታክስ በፊት ባለው ዋጋ ላይ የሚሰላ ይሆናል፤

፬. የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም የመኝታ የአገልግሎት ክፍያ የታክስ ምጣኔ ፭ (አምስት) በመቶ ይሆናል፡፡

5. About Registration

Hotel and similar accommodation service-providing establishments shall be identified and registered as follows:

1. Commercial hotel and similar service-providing establishments must register in person for accommodation service tax at the large and medium taxpayers branch offices of the revenue bureau where they pay employment income tax, salary, and rental income tax;
2. Individual taxpayers who own hotels and similar establishments must register in person for accommodation service fees at the revenue branch offices where they declare their business profit tax;
3. Hotels and similar accommodation services-providing entities must complete and declare information regarding the number of rooms prepared for accommodation and the daily price list using the registration form prepared by the revenue branch offices where they declare their taxes.

6. Payment Base and Tax rate

1. The accommodation occupancy fee of a hotel and similar service-providing establishments is the room price paid by an accommodation user for one day;
2. The price of a room in a hotel and similar service-providing establishments does not include the price of food provided by the hotel or the cost of personal services provided to the user;
3. The rate of the accommodation service fee of a hotel and similar service-providing establishments shall be calculated on the price before the Value Added Tax;
4. The tax rate for the accommodation service fee of a hotel and similar service-providing establishments shall be 5% (five percent).

Addis Ababa City Administration Revenues Bureau

ክፍል ሦስት

የመዝገብ አያያዝ፣ የደረሰኝ አጠቃቀም እና ታክስ አሰባሰብ

፯. ስለ መዝገብ አያያዝ

፩. በከተማ አስተዳደሩ የተመዘገበ ማንኛውም የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም የመኝታ አገልግሎት ሲሰጥ የተገልጋዩን መረጃ የሚመዘግብበት መዝገብ ማዘጋጀት አለበት፤

፪. የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም የመኝታ አገልግሎት ሲሰጥ የተገልጋዩን መረጃ በተዘጋጀው መዝገብ ላይ በተሟላ መልኩ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

፰. የደረሰኝ አጠቃቀም

፩. በታክስ አስተዳደር አዋጅ መሰረት የሒሳብ መዝገብ መያዝ የሚገደዱ የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም የመኝታ አገልግሎት ሲሰጥ በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ወይም በማንዋል ደረሰኝ ላይ የመኝታ አገልግሎት ክፍያ ታክስ በማካተት ገቢ ይሰበስባል፤

፪. የሒሳብ መዝገብ እንዲይዝ ለማይገደድ ማንኛውም የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም በሰጠው አገልግሎት ገቢ ላይ 70 በመቶ ተሰልቶ በ5 በመቶ ታሪፍ መሰረት በቁርጥ ታክስ እንዲከፍል ይደረጋል፤

፫. ማንኛውም የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም የመኝታ አገልግሎት ሲሰጥ ለተጠቃሚው ህጋዊ ደረሰኝ መስጠት አለበት፡፡

፱. የክፍያ አሰባሰብ

፩. የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም የመኝታ አገልግሎት ታክስ ክፍያ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀፅ (፬) መሠረት ተሰልቶ በአገልግሎት ሰጪው አማካይነት ከተጠቃሚው በህጋዊ ደረሰኝ ይሰበሰባል፤

፪. ገቢው በታክስ ነክ ማዘጋጃ ቤታዊ ገቢ አርእስት ስር በሌሎች ታክሶች ኮድ ቁጥር ፩ሺ፯፲፱ የሚሰበሰብ ይሆናል፡፡

፲. የማሳወቂያ ጊዜ

1. የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም ስለሰጠው የመኝታ አገልግሎት በየወሩ በሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ ሞልቶ የድርጅቱን ማህተም እና የሆቴል ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ ፊርማ ያረፈበት የሂሳብ ሪፖርት ምዝገባ ላከናወነበት የገቢ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ማሳወቅ አለበት፡፡
2. የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ የሆነ ሰው ስለሰጠው የመኝታ አገልግሎት በየሩብ አመቱ በሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ ሞልቶ ምዝገባ ላከናወነበት የገቢ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ማሳወቅ አለበት፡፡

Part Three

Record Maintenance, Invoice Utilization, and Tax Collection

7. Maintaining Records

1. Any hotel and similar service-providing establishment which is registered in the city administration, must prepare a register to record user information when providing accommodation services;
2. Any hotel and similar service-providing establishment must record the user's information in a complete manner in the prepared register in providing the accommodation services.

8. Invoice Utilization

1. Any hotel and similar service-providing establishments that are required to maintain books of accounts under the tax administration Proclamation shall collect revenue by including the accommodation service fee tax in the sales register machine or manual invoice when providing accommodation services;
2. Any hotel and similar service-providing establishments that are not required to maintain books of accounts shall be made to pay a lump-sum tax with five percent tariff by calculating 70 percent on the services provided;
3. Any hotel and similar service-providing establishment must issue a legal invoice to the user when providing accommodation services.

9. Payment Collection

1. The accommodation service tax payment of a hotel and similar service-providing establishments shall be calculated in accordance with Sub-Article (4) of Article 6 of this Regulation and collected from the user by the service provider using a legal invoice;
2. The revenue shall be collected under the tax-related municipal revenue title under other taxes code number 1719;

10. Declaration Period

1. Category "A" hotel and similar service-providing establishment taxpayer must declare its accommodation service monthly by filling out a report form bearing the organization's stamp and the signature of the hotel owner or manager and submit the financial report to the revenue branch office where the registration has been carried out;
2. Category "B" taxpayer must declare its accommodation service quarterly by filling out a report form and submit it to the revenue branch office where the registration has been carried out.

Addis Abeba City Administration Revenues Bureau

፲፩. የተሰበሰበውን ክፍያ ገቢ ስለማድረግ

፩. የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ ከመኝታ አገልግሎት የሰበሰበውን ማዘጋጃ ቤታዊ የታክስ ገቢ በየወሩ የተጠቃለለውን ሪፖርት መነሻ በማድረግ በግብር ከፋይነት ለተመደበበት ገቢ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ገቢ ማድረግ አለበት፤

፪. የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም የመኝታ አገልግሎት ሲሰጥ የሰበሰበውን የታክስ ገቢ ከተሰበሰበበት ወር ቀጥሎ ባለው በ፴ ቀናት ውስጥ በግብር ከፋይነት በተመዘገበበት የገቢ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት የባንክ ሂሳብ ወይም በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ዘዴ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

ክፍል አራት

ተግባርና ኃላፊነት

፲፪. የቢሮው ተግባርና ኃላፊነት

በአዋጁ ለቢሮው የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም ቢሮው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

፩. የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም የመኝታ አገልግሎት ማዘጋጃ ቤታዊ ታክስ ክፍያን በተመለከተ በከተማው ውስጥ ላሉ የመኝታ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እና ባለድርሻ አካላት ግንዛቤ እና ስልጠና ይሰጣል፤

፪. የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ የአገልግሎት ክፍያውን እንዲሰበስብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ህጋዊ ውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

፫. የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም አገልግሎቱን ሲያቋርጥ ወይም የአገልግሎት ለውጥ ሲያደርግ የሰጠውን ውክልና ያነሳል፤

፬. የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ የመኝታ አገልግሎት የክፍያ ደረሰኝ እንዲያሳትም ያዛል፤ አጠቃቀሙን ይከታተላል፤

፭. የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋሙን የመኝታ አገልግሎት ታክስ በተመለከተ ጥቆማ ይቀበላል፤ ያጣራል፤ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፤

11. Transferring the Collected Payment

1. The accommodation service provider of a hotel and similar service-providing establishments must monthly transfer the collected municipal tax revenue based on the consolidated report to the revenue branch office to which it is assigned as a taxpayer;
2. The accommodation service provider of a hotel and similar service-providing establishments must transfer the collected tax revenue within 30 days following the month of collection into the bank account of the revenue branch office where it is registered as a taxpayer or via electronic payment methods.

Part Four

Duties and Responsibilities

12. Duties and Responsibilities of the Bureau

The Bureau shall, without prejudice to the powers and responsibilities given to it as per the Proclamation, have the following powers and responsibilities for the implementation of this Regulation:

1. Create awareness and provide training regarding hotel and similar service-providing establishment accommodation service municipal tax payments to accommodation service providers and stakeholders within the city;
2. May legally delegate, as it deems necessary, hotels and similar service-providing establishments to collect the service fees;
3. Revoke the granted delegation when a hotel and similar service-providing establishment terminates its service or changes its type of service;
4. Give orders to hotels and similar service-providing establishments to issue accommodation service payment invoices; monitor the utilization of the thereof;
5. Receive and investigate reports regarding hotel and similar service-providing establishments accommodation service tax; take necessary measures;

፮. ከሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም የሚቀርብ የመኝታ አገልግሎት እንደአግባቡ በየወሩ እና በየሩብ አመቱ ገቢ ማሳወቂያ ይቀበላል፤ገቢውንም ይሰበስባል፤

፯. ከመኝታ አገልግሎት ታክስ ክፍያ ጋር በተያያዘ የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ ለሚያጋጥመው ችግሮች መፍትሔ ይሰጣል፤

፰. በየሩብ ዓመቱ ከሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም የሚቀርበውን የመኝታ አገልግሎት ታክስ ክፍያ አሰባሰብ ሪፖርት እና የሂሳብ ሰነድ ይመረምራል፤ ኦዲት ያደርጋል፤

፱. የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋሙን የመኝታ አገልግሎት ክፍያ አሰባሰብ በአካል በመገኘት ወይም የገቢ ሰነድ በማስቀረብ ይመረምራል፤ ውሳኔ ይሰጣል፤

፲. የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ የመኝታ አገልግሎት ለመመዘገብ ያዘጋጀውን መዝገብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ መዝገቡን ያስቀርባል፤ ይመረምራል፤ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፲፫. <u>የከተማ አስተዳደሩ ቱሪዝም ኮሚሽን ተግባርና ኃላፊነት</u>

በአዋጁ ለኮሚሽኑ የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም ኮሚሽኑ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

፩. ቢሮው የባለ ኮከብ ሆቴል፣ ሆቴል፣ ሪዞርት፣ ሎጅ፣ ሞቴል፣ እንግዳ ማረፊያ እና ፔንሲዮን መረጃ ጥያቄ ሲያቀርብ መረጃውን ይሰጣል፤

፪. በሆቴሎች ላይ የሚደረጉ የደረጃ ለውጦችን ለቢሮው ያሳውቃል፤

፫. አዲስ ወደ ሆቴል ዘርፍ የሚቀላቀሉ ድርጅቶችና ግለሰቦችን በወቅቱ ለቢሮው ያሳውቃል፤

፬. ሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሙያ ፈቃድ ለማሳደስ ሲቀርቡ የወቅቱን የመኝታ አገልግሎት ማዘጋጃ ቤታዊ ታክስ የከፈሉ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ከገቢዎች ቢሮ እንዲያቀርቡ ያደርጋል፤

6. Receive monthly and quarterly, as deems relevant, accommodation services revenue declarations from hotel and similar service-providing establishments; collect the revenue
7. Provide solutions to challenges encountered in connection with hotel and similar service-providing establishment accommodation service tax payments;
8. Examine the quarterly submitted accommodation service tax payment collection reports and financial documents of hotels and similar service-providing establishments; audit the thereof;
9. Examine accommodation service tax payment collection ways of hotels and similar service-providing establishments in person or through demanding revenue documents; make decisions;
10. Demand the presentation of the register that was prepared for the registration of hotel and similar service-providing establishments' accommodation service in order to verify its accuracy and examine same; make decisions.

13. <u>Duties and Responsibilities of the Tourism Commission of the City Government</u>

The Commission shall, without prejudice to the powers and responsibilities given to it as per the Proclamation, have the following powers and responsibilities for the implementation of this Regulation:

1. Provide information regarding star hotels, hotels, resorts, lodges, motels, guest houses, and pensions for the bureau upon its request;
2. Notify any category changes made to hotels to the bureau;
3. Timely notify new businesses and individuals joining the hotel sector to the bureau;
4. Require hotels and similar service-providing establishments to submit a letter from the revenues bureau confirming that they have paid the latest accommodation municipal tax, when they require renewing their professional licenses.

፲፬. የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም ተግባር እና ኃላፊነት

ማንኛውም የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም መኝታ አገልግሎት ሰጪነት የተሰማራ ማንኛውም ሰው፡-

፩. መመዝገብ አለበት፤

፪. የመኝታ ክፍል አገልግሎት ሲሰጥ የተገልጋዩን መረጃ የሚመዘግብበት መዝገብ ያዘጋጃል፤ መረጃውን ይመዘግባል፤

፫. አገልግሎት የሚሰጡ ክፍሎች ብዛትን እና የሚያከራዩበትን ዋጋ ያስመዘግባል፤

፬. የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽኑ እና ደረሰኙ ላይ የመኝታ አገልግሎት የማዘጋጃ ቤታዊ ታክስ የሚል እንዲካተትበት ያደርጋል፤

፭. አገልግሎቱን በሰጠበት ወቅት ለተጠቃሚው ህጋዊ ደረሰኝ ይሰጣል፤ ገቢውን ይሰበስባል፤

፮. የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ የገቢ ማሳወቂያ ሪፖርት በየወሩ ምዝገባ ላከናወነበት የገቢ ሰብሳቢ ተቋም ያሳውቃል፤ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ የሆኑ የሆቴልና መሠል አገልግሎት ሰጪ ሰው በቁርጥ መክፈል የሚገባውን የማዘጋጃ ቤታዊ ታክስ ገቢ በየሩብ ዓመቱ በግብር ከፋይነት ለተመደቡበት ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ገቢ ማድረግ አለበት፤

፯. የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ /ድርጅት/ በየወሩ የተጠቃለለውን ሪፖርት መነሻ በማድረግ የተሰበሰበውን ክፍያ ገቢው ከተሰበሰበበት ወር ቀጥሎ ባለው በ፴ ቀናት ውስጥ በግብር ከፋይነት ለተመዘገበበት የገቢ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት የባንክ ሂሳብ ወይም በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ዘዴ ገቢ ማድረግ አለበት፤

፰. የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ የተጠቃለለውን ሪፖርት መነሻ በማድረግ የሰበሰበውን ገቢ በየሩብ አመቱ በግብር ከፋይነት በተመዘገበበት የገቢ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት የባንክ ሂሳብ ወይም በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ዘዴ ገቢ ማድረግ አለበት፤

፱. ለተገልጋዮች በግልጽ በሚታይ ቦታ የአስተያየት እና ጥቆማ መስጫ ስልክ ቁጥር መለጠፍ አለበት።

ክፍል አምስት

ስለ ቅሬታ አቀራረብና ውሳኔ አሰጣጥ

፲፭. ስለ ተገልጋይ ቅሬታ አቀራረብ

ከሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም የመኝታ አገልግሎት ማዘጋጃ ቤታዊ ታክስ ክፍያ ጋር የተያያዘ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ተገልጋይ ለቢሮው በስልክ ወይም በአካል በመገኘት ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል።

14. Duties and Responsibilities of Hotels and Similar Service-Providing Establishments

Any person engaged as an accommodation service provider in a hotel or similar service-providing establishment should:

1. be registered;
2. Prepare a register to record user's information when providing accommodation services; record the information accordingly;
3. Ensure the registration of available rooms and their prices;
4. Make sure that the phrase "Accommodation Municipal Tax" is included in the sales register machine and invoices;
5. Issue a legal invoice to the user while providing the service; collect the revenue;
6. Category "A" taxpayer must declare its revenue reports monthly to the revenue collecting organ where it is registered as a taxpayer; Category "B" hotels and similar service-providing persons must transfer the municipal tax revenue due under lump-sum tax quarterly to the branch office where they are assigned as taxpayers;
7. Category "A" taxpayer (organ) must, based on the consolidated monthly report, transfer the collected payment, within 30 days following the month of collection into the bank account of the revenue branch office where it is registered as a taxpayer or via electronic payment methods;
8. Category "B" taxpayer must, based on the consolidated report, transfer the collected payment, quarterly into the bank account of the revenue branch office where it is registered as a taxpayer or via electronic payment methods;
9. Post a telephone number for suggestion and reporting purpose in a visible manner for customers.

Part Five

Complaint Submittal and Decision Making

15. Complaint Submission of Customers

Any customer who has a complaint regarding accommodation service municipal tax payment of a hotel and similar service-providing establishment may submit his complaint to the bureau either by phone or in person.

፲፮. ስለ አገልግሎት ሰጪ ቅሬታ አቀራረብ

፩. በአገልግሎት ክፍያ አሰባሰብ እና በአሰራር ሂደት ላይ ቅሬታ ያለው የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም በየደረጃው ባለው የቅሬታ ሰሚ አካል ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፤

፪. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ቅሬታ አቅራቢ ለከተማ አስተዳደሩ ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

፲፯. ስለ ቅሬታ አፈታትና ውሳኔ አሰጣጥ

፩. ማንኛውም የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም የታክስ ውሳኔው በደረሰው በሃያ አንድ ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ታክሱን በሚከፍልበት የገቢ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ለሚገኝ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታውን ሊያቀርብ ይችላል፤

፪. ቅሬታ ሰሚው ኮሚቴ ቅሬታውን ከተቀበለ ባሉት ፲፭ ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፤

፫. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው በሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ማንኛውም የማዘጋጃ ቤታዊ ታክስ ከፋይ ይግባኙን ለከተማ አስተዳደሩ የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ውሳኔው በተሰጠ ፴ ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ለማቅረብ ይችላል፡፡

፲፰. ስለቅጣት

፩. ማንኛውም የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም ከመኝታ አገልግሎት የተገኘን ገቢ ወቅቱን ጠብቆ ሪፖርት አለማሳወቅ ለዘገየበት በየወሩ ፭ ከመቶ ከክፍያው ከ፶ ከመቶ ያልበለጠ ቅጣት እንዲከፍል ይደረጋል፤

፪. ማንኛውም የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም የመኝታ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በውክልና የተሰበሰበውን ክፍያ ገቢ ሳያደርግ ከዘገየ መክፈል ከነበረበት ቀን ጀምሮ የሚታሰብ የኢትዮጵያ የንግድ ባንኮች የወቅቱ ማበደሪያ ወለድ ምጣኔ እና የወለዱ ፲፭ ከመቶ ተጨምሮበት ወለድ እንዲከፍል ይደረጋል፤

16. Service Providers Complaint Submission

1. Any accommodation service provider of a hotel or similar service-providing establishment who has a complaint regarding the collection of service fees and operational procedures may submit his complaint to the complaint hearing body at each level;

2. Any complainant who is dissatisfied with the decision of the complaint hearing committee may submit his appeal to the tax appeal commission of the city administration.

17. Complaint Resolution and Decision Making

1. Any hotel and similar service-providing establishment may submit its complaint to the complaint hearing committee at the revenue branch office where it pays taxes within twenty-one consecutive working days from the date of receiving the tax decision;
2. The complaint hearing committee shall make its decision within 15 consecutive working days after accepting the complaint;
3. Any municipal taxpayer who is dissatisfied with the decision of the complaint hearing committee may submit his appeal to the tax appeal commission of the city administration within 30 consecutive working days from the date the decision was rendered.

18. Penalties

1. Any hotel and similar service-providing establishment that fails to timely declare revenue reports generated from accommodation services shall be penalized 5% per month for the delayed period, not exceeding 50% of the total payment due;

2. If any hotel and similar service-providing establishment accommodation provider delays transferring the collected fees under delegation, it shall be liable to pay an interest calculated from the date of late payment was due based on the current lending interest rate of commercial banks plus an additional 15% of the interest amount.

Addis Ababa City Administration Revenues Bureau

፫. ማንኛውም የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም ከመኝታ አገልግሎት የተገኘን የገቢ መረጃ ከደበቀ እና/ወይም የሀሰት የገቢ ካቀረበ በወንጀል ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፤

፬. ማንኛውም የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋም በዚህ ደንብ የተደነገጉትን በመጣስ ሌሎች ድርጊቶችን በመፈጸም ጥፋት ሲፈጽም ከተገኘ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፱፻፷፫/፪ሺ፲፰ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል።

፲፱. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው ይህንን ደንብ ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት።

፳. <u>ተፈፃሚነት ስለማይኖረው ህግ</u>

ይህን ደንብ የሚቃረን ካቢኔው ያወጣው ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

፳፩. <u>መመሪያ ስለማውጣት</u>

ቢሮው ይህን ደንብ ለማስፈፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

፳፪. ይህ ደንብ ሰኔ ፲፱ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፲፱ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም

አዳነች አቤቤ ደሳ
የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

3. Any hotel and similar service-providing establishment accommodation provider that conceals income related information and/or submits fraud revenue declarations regarding accommodation services shall be held criminally liable under the criminal law;

4. If any hotel and similar service-providing establishment violates the provisions specified under this Regulation or commits other offenses, it shall be held liable in accordance with the tax administration Proclamation No. 983/2016.

19. <u>Duty to Cooperate</u>

Any person is duty bound to cooperate for the implementation of this Regulation.

20. <u>Inapplicable Laws</u>

Any Regulation, directive, or customary practices issued by the council of the city which are inconsistent with this Regulation shall have no effect on matters covered under this Regulation.

21. <u>Power to Issue Directives</u>

The bureau may issue directives for the implementation of this Regulation.

22. <u>Effective Date</u>

This Regulation shall enter into force as of this 19th day of June 2026.

Done at Addis Ababa, this 19th day of June 2026.

Adanech Abiebie
Mayor of Addis Ababa City